# አንድነትን ጨምሮ የተቃዋሚ መሪዎች በኔዘርላንድ ኤምባሲ ዉይይት አደረጉ !

## አንድነት - ምርጫዉ ነጻና ፍትሃዊ ካልሆነ አልሳተፍም አለ።

## ልዩ ዘገባ ከአወደ ኢትዮጵያ

ሰኔ 4 ቀን 2001 ዓ.ም

የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ (አንድነት) ፓርቲ አመራር አባል ኢንጅነር ግዛቸው ሽፈራው፣ የፓርቲው ም/ል ሊቀመንበርና የድርጅት ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ፣ በትናንትናው ዕለት ሰኔ 3 ቀን 2001 ከኔዘርላንድ ከመጡት የሰብአዊ መብት አምባሳደር ከሆኑት፣ ያን ሃምበርገር ጋርና እንዲሁም ከኤምባሲው የኔዘርላንድ አምባሳደርና በኔዘርላንድ ኤምባሲ የልማት ትብብር ክፍል ም/ል ሃላፊ ከሆኑት ጋር ውይይት አካሂደዋል፡፡

ኢንጅነር ግዛቸው ሽፈራው በኤምባሲው የተገኙት ፓርቲያቸውን አንድነትን ወክለው ነበር። ንግግሩ በይፋ ከመጀመሩ አስቀድሞ በውይይቱ ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑ የተጠሩት የተለያዩ ተቃዋሚ ፓርቲ አባላት ተገኝተው ሳለ፣ ንግግሩ ከመጀመሩ አስቀድሞ የአንድነት ም/ል ሊቀ መንበር ኢንጅነር ሽፈራው «ቀደም ብሎ ከኤምባሲው ጋር የተደረገው ውይይት የተደረሰበት ስምምነት የተከበረ ባለመሆኑ፣ በዚህ ውይይት ላይ መካፈል አልችልም። ስለዚህም የፓርቲዬን በሃገራችን የሰብአዊ መብት ሁኔታ የሚገልጸውን ጽሁፍ ሰጥቼ እንድሄድ ይፈቀድልኝ» በማለት ሲያስረዱ፣ እሳቸውን በመከተል ክቡር ዶር ነጋሶ ጊዳዳና አቶ ገብሩ አስራትም ሃሳቡን በመደገፍ «እኛ ተቃዋሚዎች ነን። ስለዚህም ከገዢው ፓርቲና የገዢው ፓርቲ ተቀጥላ ከሆኑት ተቃዋሚ ነን ከሚሉት ጋር ቁጭ ብለን የምናደርገው እውነቱን ማብራራት ሳይሆን ክርክር የምንገጥምበት ስለሚሆን፣ እኛም እንደ «አንድነት« በስብሰባው ላይ መሳተፍ ይቸግረናል በማለት አሳሰቡ።

ቀደም ብሎ በዚህ ጉዳይ ላይ ኢንጅነር ግዛቸው ያላቸውን አስተያየት ተጠይቀው፣ ሁሉንም በአንድ መድረክ ማቅረቡ ውጤት እንደማይኖረውና ክርክር እንደሚሆን በመግለጽ፣ ተቃዋሚዎችን ለብቻቸዉ ገዢውን ፓርቲና ደጋፊዎቹን ደግም ለብቻቸዉ ማናገር እንደሚሻል ያቀረቡት ሃሳብ ተቀባይነት አግኝቶ ስለነበር ነዉ ወደ ኤምባሲው የሄዱት።

በመጨረሻም አንደኛው ተሰብሳቢ፣ የታወቁት የገዢው ፓርቲ ደጋፊና ቤተኛ የሆኑት አቶ ልደቱ አያሌው፣ የሚባለውን ሁሉ ካዳመጡና ጉዳዩ በሳቸው ላይ ያነጣጠረ መሆኑ ስለገባቸው «ችግሩ እኔ ስለሆንኩ እኔ ስብሰባውን ባልካፈል ስለሚሻል ብወጣ ይሻላል» ብለው ስብሰባውን ለቀው በመወጣታቸዉ የተቀሩት ስብሰባዉን ሊቀጥሉ ችለዋል።

ስብሰባው እንደተጀመረ የመጀመያው ተናጋሪ የሆኑት የአንድነት ም/ሊቀ መንበርና የድርጅት ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ኢንጅነር ግዛቸው ሽፈራው፣ ገዢው ፓርቲ ለዲሞክራሲና ለሰብአዊ መብት ያለው አመለካከት የተበላሸና ኢፍትሐዊ እንደሆነ፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን እያዋከበና ቢሯቸውን እያፈረሰ በየክልሉ ያሉ ሃላፊዎችን እያሰረና እያባረረ እንደሆነ፣ በዝርዝር በጽሁፍ አቅርበው ካስረዱ በኋላ በፎቶግራፍ የተደገፈውን ማስረጃ አርበዋል።



ይህ የአንድነት ቢሮ ነው። በገዢው ፓርቲ ካድሬዎችና ታጣቂዎች የፈረሰውና አባላቱም ከአካባቢው የተባረሩበት።

በጸሁፉና በውይይቱ ላይ ግንባር ቀደም ሆኖ የቀረበው፣ የፓርቲው መሪ የወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ አለአግባብ መታሰር ሲሆን ፣ ጉዳዩንም በተመለከተ ዝርዝር ዘገባም አቅርበዋል።

የኔዘርላንድ ኤምባሲ አባላት የተባለውን ካዳመጡ በኋላ ጥያቄዎች አንስተዋል።

ከቀረቡትም ጥያቄዎች

1. እናንተ መንግሥት ብትሆኑ ለሕዝቡ የምታቀርቡት ምን የተለየ ነገር አለ ?
2. በሚመጣው ምርጫ ላይ ያለአንዳች ቅድመ ሁኔታ ትካፈላላችሁ ወይ?
3. የሕዝቡ ቁጥር እየጨመረ ነውና ድህነትን ከቁጥሩ መጨመር ጋር እንዴት ትዋጉታላችሁ?
4. ዲያስፖራው በሰላማዊ ትግል አያምንምና እናንተስ ምን ትላላችሁ?

የሚል ነበሩ።

እንጂነር ግዛቸው ለተጠየቁት ጥያቄ የሰጡት መልስም እንደሚከተሉት ቀርበዋል።

1. የኢትዮጵያችን ትልቁ ችግር የዴሞክራሲና የዴሞክራሲ ተቀዋማት እጦት ነውና እኛ ደግሞ በአገራችን እውነተኛና ትክክለኛ ዴሞክራሲን ለሕዝቡ እናቀርባለን።

2. አንድነትና እዚህ ያለነው ፓርቲዎች በሙሉ የምርጫ ፓርቲዎች ነን። በሕዝብ ድምጽ፣ በሕዝብ ፍላጎት፣ በሕዝብ የምርጫ ውጤት እናምናለን። ያም ሆኖ ግን፣ ግባችን ምርጫው ሳይሆን ከምርጫው በኋላ የሚፈጠረው ስርአት ነው። ያን ለማድረግ ደግሞ ምርጫው ፍትሃዊ ነፃና ዴሞክራሲያዊ መሆን አለበት። ያ ካልሆነ ግን አንድነት በምርጫው አይሳተፍም።

3. የሕዝቡ ቁጥር ከልማት ጋር መጣጣም አለበት። ይህንንም ለማድረግና ከድህነት ለመላቀቅ አስፈላጊውን መድረክ እንፈጥራለን። በቃላት ሳይሆን በተግባር ሊተረጎም የሚችል በባለሙያዎች የተጠና መፍትሔ ሕዝቡ አምኖ የሚቀበለውና ለተግባራዊነቱ የሚሰለፍበት መድረክ።

4. «እኛ በዳያስፖራ ጠንካራና ደጋፊዎች አሉን። በብዛት። ታዲያ የኛ ደጋፊዎች የሚደግፉን የኛን እምነት ይዘው፣ እኛም የነሱን ፍላጎት አካተን ነው። ለሰላማዊ ትግል ነው የቆምነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰላማዊ ትግልን ነው የሚፈልገው። ከሰለጠነ ፖለቲካ የሚወጣውም ሰላማዊ ትግል ነው። ሌላ የትግል ስልት የሚከተሉ ቢኖሩም ዳያስፖራው በጥቅሉ የአመጽ መንገድ የተከተለ ነው ማለት አይቻልም። በዲያስፖራው አካባቢ ለምን ሌላ የትግል ስልት የሚከተሉ ተፈጠሩ ለሚለው ይህንንም የፈጠረው ኢህአዴግ እራሱ ነው። ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ፣ የሰላማዊውን ትግል በር በሃገር ውስጥ ሲዘጋ፣ ተቃዋሚዎችን ሲያዋክብ፣ ቢሯቸውን ሲዘጋ፤ አላላውስ ሲል፣ አማራጭ በማጣት ተገፍተው ወደዚያ የሄዱ ናቸዉ ማለት ይቻላል።

   በማለት ኢንጅነር ግዛቸው ግልጽ የሆነውን ዕውነታ አስቀምጠዋል። ሌሎችም ተሳታፊዎች የኢንጅነር ግዛቸውን ሃሳብ በመደገፍና ተጨማሪ ማብራሪያ በመስጠት ለልኡካኑ አስፈላጊውን ዘገባ አስጨብጠዋል።

   ይህ የአንድነት ቢሮ ነው። በገዢው ፓርቲ ካድሬዎችና ታጣቂዎች የፈረሰውና አባላቱም ከአካባቢው የተባረሩበት።